የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ትምህርት ቢሮ

በ2019 ዓ.ም በ11ኛ ክፍል የሥራና ተግባር ትምህርት በከተማ ደረጃ በተመረጡ አዲስ ለሚጀመረው የሙያ ዓይነቶች የአተገባበር ማኑዋል

ጥቅምት ወር 2019ዓ.ም

ትምህርት ቢሮ

ይዘት

መግቢያ

ተግባርና ኃላፊነት

አስፈላጊነት

የትምህርት ቢሮ

ዓላማ

የክፍለ ከተማ

የሙያ ዓይነት አመራረጥ ሂደት

የትምህርት ቤት

የአፈጻጸም ስልቶች

ማጠቃለያ

መግቢያ

የትምህርት ፍኖተ ካርታ ስለ ሥራና ተግባር ትምህርት

- የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናት እንዳሳየው የአጠቃላይ ትምህርት **ቀለም ትምህርት** ላይ ያተኮረ እንደነበረ
- የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርቱ ክፍተቶች በዝርዝር ሲታዩ **ሀገር በቀል እውቀት ፣ የሙያ ትምህርት** እና **የግብረገብ ትምህርት** እንደሚጎድለው፤
- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጨርሰው ወደ ከፍተኛ ትምህርት **መግባት ያልቻሉ** ከመሆንም በላይ **ሙያ ትምህርት ለማሰብ ምንም ግንዛቤ** አልነበራቸውም
- በዚህም ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን የሚጨርሱ ወጣቶች **መሠረታዊ እውቀት** የጨበጡ ነገር ግን **ሥራ የማይፈጥሩ** እና **የተማሩ ሥራ አጦች** እንዲሆኑ አድርጓቸዋል

የቀጠለ

- በምክረ ሃሳብም ይህን ችግር በመሠረታዊነት ለመቅረፍ ሥራ ፈጣሪ ዜጐችን ለማፍራት ከቀለሙ ትምህርት **ጎንለጎን በሁለም የትምህርት ደረጃዎች የሙያ ትምህርት** እንዲሰጥም የትምህርት ፍኖተ ካርታ አመላክቷል፤
- በዚሁ መሰረትም የሥራና ተግባር ትምህርት **7ኛ እና 8ኛ ክፍል** እንደ አንድ ትምህርት ፤ በሁለተኛ ደረጃ **11ኛ እና 12ኛ አንድ የሙያ አይነት** መርጠው እንዲማሩ ማድረግ ፤
- ወደ ትግበራ በመሸጋገር ላይ ቢሆንም የትኩረት ዘርፎችና የሙያ አይነቶች **በጥንቃቄ ልየታ መደረጉ**፤

ይህ የአተገባበር ማንዋልም ተዘጋጅቷል።

የማኑዋሉ አስፈላጊነት

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት እና የአካባቢ ጸጋን ግንዛቤ በማስገባት የሚተገብሯቸውን የሙያ አይነቶችን እንዲለዩ ለማስቻል፣

- የሰው ሃይልና ግብዐቶችን እያሟሉ ትምህርቱን እንዲጀምሩ ለማድረግ፣

- የፈጻሚና ባለድርሻ አካላት **ተግባርና ሀላፊነታቸውን ተገንዝበው** አጀማመርን በቅንጅት ውጤታማ ለማድረግ፣

- አሰልጣኝ መምህራንን ለመመልመልና ለመመደብ

የቀጠለ

- የተለዩ የሙያ ዓይነቶችን በሁሉም ትምህርት ቤቶች በአንድ ጊዜ ለመጀመር ከፍተኛ ግብዓት የሚጠይቅ በመሆኑ በቀላሉ ሊሟሉ የሚችሉትን በማሟላት ሌሎችን በሂደት እያሟሉ ትምህርቱን ለማስጀመር፣
- በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በወጥነት የስራና ተግባር ትምህርት መርኃ ግብርን በነባሩ እና በተጨመሩ የሙያ ዓይነቶች በከተማ ደረጃ ልየታ የተደረገ ስለሆነ በወጥነት ለማስጀመር ፣

የማኑዋሉ ዓለማ

- በአንድ ትምህርት ቤት ሊሰጡ የሚችሉ ተጨማሪ የሙያ ዓይነቶችን በአካባቢው ጸጋ ልየታ ለማድረግ፤
- የሙያ ትምህርቶችን ለመተግበር አስፈላጊ ግብዓቶችን ለመለየት እና ለማሟላት።
- በተመረጡት የሙያ ዓይነቶች ውስጥ ተማሪዎች በአካባቢያዊ ኢኮኖሚና ትምህርት ቤት አቅም መሰረት የሚመረጥ አማራጭ እንዲኖራቸው።
- የሥራና ተግባር ትምህርት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በምክኒያታዊነት እና በወጪ ቆጣቢነት እንዲተገበር።

የመጀመሪያ ዙር አተገባበር

- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ 49876 ተማሪዎች በደረጃ-አንድ በሚሰጠው ትምህርት ሙያ መመረቃቸው፤
- 12 ከነበረው የሙያ ትምህርት ውስጥ 11ዱን ተግባራዊ መደረጉ፤

በልምምድ ላይ

ለትግበራ ዝግጁ የሆኑ የሙያ ዓይነቶች

- በ2017 ዓ.ም ከ12 የሙያ ትምህርቶች ውስጥ በ11 ሙያየ መስክ ላይ ተግባር ውስጥ ተገብቷል፤
- በ2019 ዓ.ም 11 የሙያ ትምህርቶች ተልኳል፤ይህንን ወጥነት ባለው ለመተግበር

በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የሙያ ትምህርት ከቴክኒክና ሙያ ከሚሰጠው ስልጠና ያለው የስርዓተ ትምህርት ግንኙነት ዶክመንት ሪቪው

ግኝቱ

- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጠው ደረጃ አንድ በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ደረጃ ሁለት አለመስጠት፤
- የሙያው ስልጠናው ጊዜው ተመጣጣኝ አለመሆን፤
- በመንግስት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የማይሰጥ የሙያ መስክ መኖሩ፤
- አብዛኛው ይዘቶቹ በከፊል ግንኙነት መኖሩ ናቸው።

የሙያ ትምህርቶቹም

- በአጠቃላይ 23 የሙያ ትምህርቶች አሉ። እነሱም

No	In 2019 E.C New CTE
1	Meta work Technology
2	Automotive Technology
3	Garment Technology
4	Building Electrical Installation
5	Plumbing Installation
6	Soft Ware Development
7	Crop Production
8	Health Caregiving
9	Hotel Operation
10	Hair Dressing and Beautification
11	Food Preparation

No	In 2017 E.C New CTE
1	Woodwork Technology
2	Finishing Construction Works
3	Web Design and Development
4	Computer Maintenances & Networking
5	Animal Production
6	Natural Resource Management
7	Community Health Service
8	Journalism
9	Psychosocial care Giving
10	Accounting and Finance
11	Marketing and sales management
12	Vocal Performance & Dance

- ዳሰሳውን መሰረት በማድረግ በከተማ ደረጃ አዋጪ የሉኦትን የሙያ ትምህርቶችን ልየታ ተደርጓል።
- የመምህራንን ፖሮፋይል መሰረት በማድረግ ቅጥር የሚገኝባቸውን ልየታ ተሰርቷል፤
- ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ያለውን የሰው ኃይልና ግብዓቶችን ተለይቷል፤
- ገበያው የሚፈልገውን የሙያ መስክ መሰረት በማድረግ ተለይቷል። በዚሁ መሰረት

በ2019ዓ.ም ሊተገበሩ የጠመረጡ ሙያ ትምህርቶች

No	Career cluster	Career pathways	Remark
1	Manufacturing	Woodwork Technology	
		Metal work Technology	New
2	Building construction	Finishing Construction Works	
		Building Electrical Installation	New
		Plumbing Installation	New

የቀጠለ

No	Career cluster	Career pathways	Remark
4	Agriculture science	Animal Production	
5	Health Science	Community Health Service	
6	Communication and social science	Journalism	
7	Business science	Accounting and Finance	
		Marketing and sales management	
		Hotel Operation	New
8	Performing and visual Arts	Vocal Performance & Dance	

የሙያ ዓይነት አመራረጥ ሂደት

በ2019ዓ.ም የሥራና ተግባር ትምህርት ለ11ኛ ክፍል በነባሩ እና በአዲስ መልክ የሚጨመሩ የሙያ ዓይነቶች የአመራረጥ ሂደት ከዚህ በታች ባለው መሰረት ይከናወናል።

- ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በከተማ ደረጃ በተለዩ በሙያ መስክ ላይ ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ።
- አዲስ የተጨመሩ ሁሉንም የሙያ አይነቶች አሟልቶ በአንድ ትምህርት ቤት በአንድ ጊዜ ለመተግበር ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቅ የሚመረጡ የሙያ ዓይነቶች በትምህርት ቤት ደረጃ በጥንቃቄ መምረጥ፤

- ትምህርት ቤቶች የሙያ አይነቶችን ሲመርጡ በትምህርት ቤቱ አካባቢ ያለውን ምቹ ሁኔታ ማለትም ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ ግብዓቶች መኖራቸውን ፣ የሙያ ዓይነቱን ሊያስተምሩ የሚችሉ በሙያ ዓይነቱ ምሩቃን መኖራቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት፤
- ትምህርት ቤቶች ሙያውን ሲመጡ በአቅራቢያቸው ካሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጥና ግብዓትን በጋራ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ መኖሩን ታሳቢ ይደረጋል፤

- የሙያ ዓይነቶች ብዛት እንደ ትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ፍላጎት፣ብዛት፣የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና መምህራን የመሟላት እንደሚቻል በአግባቡ መታየት ይገባል፤
- በ11ኛ ክፍል የሚጀምረውን አዲስ ሙያ ዓይነቶች ቀድሞ ሲሰጥ የነበረው ላይ በተጨማሪነት መሆኑን ታሳቢ ማድረግ
- ተማሪዎች የሚመርጡት ተጨማሪ የሙያ ዓይነት ከራሳቸው ፍላጎትና ችሎታ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት።

የቀጠለ

- አንድ ተማሪ አንድ የሙያ ትምህርቶች ብቻ ይሰለጥናል፤
- ተጨማሪ የሙያ ትምህርቶች ብዛት እንደትምህርት ቤቶች ሁኔታ ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል።
- የ11ኛ ክፍል የሚከፈቱን የሙያ ትምህርቶች የአካባቢውን ጸጋ ፤ የስራ ዕድል እና የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ይፈጸማል፤
- ትም/ቤቶች የሙያ ትምህርቶች ልየታ ካደረገ በኋላ ለትም/ቤቱ ማኔጅመንት አቅርቦ ማጸደቅ ይኖርባቸዋል። ውጤቱንም በሪፖርት በየደረጃው ማቅረብ ይጠበቃል፤

የአፈጻጸም ስልቶች

- የሙያ ትምህርቶችን ለማስጀመር በሚደረገው የመለየት ስራ ከመምህራንና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበትና በትብብር ይሰራል።
- የሙያ ትምህርቶችን የትምህርት አመራረጥ በትምህርት የበላይ አመራሩ የቅርብ ክትትል እንዲፈጸም ይደረጋል።

ተግባርና ኃላፊነት

1. ትምህርት ቢሮ

- የሙያ ትምህርቶች ለማስጀመር መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል።
- የሙያ ትምህርቶች ልየታ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ይከታተላል ፤ ይደግፋል።
- የሙያ ትምህርቶች የሁኔታ ትንተናና አጀማመር ሪፖርት በማጠናቀር ለትምህርት ሚኒስቴር ይልካል።
- ከቴክኒክና ሙያ ቢሮና የሚመለከታቸው አካላት ጋር ትስስር በመፈጸም ይተገብራል፤

2. ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት

- የሙያ ትምህርቶች ለማስጀመር መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል።
- የሙያ ትምህርቶች ልየታ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ይከታተላል ፤ ይደግፋል።
- ትምህርት ቤቶች የሙያ ትምህርቶችን ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ በሚተነትኑበት ወቅት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።
- የሥራና ተግባር ትምህርትን የሚመራና የሚከታተል ባለሙያ ይመድባሉ ፤ ወደ ስራ ያስገባል።
- በትምህርት ቤቶች ተዘጋጅቶ የተላከውን የሙያ ትምህርቶች አጀማመር የሙያ አይነት የሁኔታ ትንተና እና ሪፖርት በማጠናቀር ለትምህርት ቢሮ ይልካል።

3. የትምህርት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- የሙያ ትምህርት ለማስጀመር የሚያገለግል ዕቅድ ያዘጋጃል።
- ለሙያ ትምህርቶች የሁኔታ ትንተና ከባለድርኛ አካላት ጋር ያከናውናል።
- የተዘጋጀውን የሙያ አይነቱ የሁኔታ ትንተና ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል።
- የሚሰጥባቸውን የሙያ ትምህርቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይወስናል።
- የተለዩ የሙያ ዓይነቶችን ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤ ሪፖርት ያደርጋል።

- በአቅራቢያ ያሉት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ያሉትን ግብዓቶች ይለያል፤
- ከኮሌጆችና የሙያ ትምህርቶችን ሊደግፉ የሚችሉ ተቀሚት ጋር ትስስር ይፈጥራል፤

የአፈጻጸም አቅጣጫ

- ክፍተትን መሰረት ያደረገ ለአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል
- ሁሉም ተግባር በእቅድ ይመራል፤
- የአካባቢውን ጸጋ ልየታ ይደረጋል፤
- ለሙያ ትምህርቶች ለመተግበር ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
- የተሸለ አፈጻጸም ካላቸው ትምህርት ቤቶች ልምድ ልውውጥ ይደረጋል፤
- የመምህራን ቅጥር ይፈጸማል፤

ማጠቃለያ

- የሥራና ተግባር ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ትምህርት ቤቶች በአካባቢያቸው ያለውን ጸጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ከሚመለከታቸው ባለደርሻ አካላት ጋር በተለይም ከትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በመመካከር ይጀምራል።
- የሙያ ዓይነቶች በየአካባቢዉ የሚሰሩ የግል ባለሃብቶች፣ የመንግስት ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሮች የትምህርቱን አላማ በማስረዳት አስፈላጊ ግብአት ለሚሟላትና ለቀጣይ ስራዎች የትብብር መንፈስ መፍጠር ይገባል።

አመሰግናለሁ